20ኛ ዓመት ቁጥር 4
20th Year No. 4

ባሕር ዳር ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም
Bahir Dar, February 03, 2015

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 35.60 ብር
Unit Price Birr 35.60

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 223/2007 ዓ.ም የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ	Proclamation No.223/2015 The Amhara National Regional State Courts Establishment Revised Proclamation

አዋጅ ቁጥር 223/2007 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በሕግ የበላይነት፣ በግልፅነትና በተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ይበልጥ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No.223/2015

A Revised Proclamation Issued to Provide for the Amahara National Regional State Courts

WHERE AS, it has become necessary to further strengthen Courts of the Amhara National Regional State so that they can provide efficient, effective and accessible judicial service based on the principles of rule of law, transparency and accountability thereof;

የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሻለ አገልግሎት በመስጠት የሕዝብ አመኔታን ማግኘት ይቻላቸው ዘንድ አደረጃጀታቸውን፣ አሰራራቸውንና እንደተገቢነቱም የዳኝነት ስልጣናቸውን ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታው በሚጠይቀው መጠን ማስተካከልና ከስራን መልሶ ማደራጀት ጥናትና ካደጉ ሃሳቦች ጋር አገናዝቦ መከለስ በማስፈለጉ፤

WHERE AS, it is found necessary to adjust the organization, working system and jurisdiction of courts of the region, as deems appropriate to the extent of objective economic reality, as well as to revise same in view of the study of business process reengineering and developed ideas, so that they can get public trust by providing a better service;

በየደረጃዉ ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች በተጓዳኝ ለሚገኙ የሕዝብ ምክር ቤቶች የዳኝነት ሥራ አፈጻጸማቸዉን በተመለከተ የዳኝነት ነጻነትን በማይጻረር ሁኔታ በዘገባ እንዲያሰሙ ማድረጉ የተቋማቱን ግልጽነትና ተጠያቂነት ይበልጥ ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ በመታመኑ፤

WHERE AS, it is believed that requiring regional courts at different levels to report the performance of their judicial activity, without contravenning the judicial independence, to parallely found public councils, has a greate contribution to further ensure the transparencey and accountability of the same;

የክልሉን ፍርድ ቤቶች አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያት የወጡትን የማሻሻያ አዋጆች መከለስና በአንድነት ማጠቃለል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHERE AS, it is deemed necessary to revise and consolidate the various amendment proclamations, issued at different times, with regard to courts of the region, into one;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ የክልሉ ሕገ- መንግስት አንቀጽ /49/ ንዑስ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub –article 3/1/ of the Revised Regional Constitution, the Council of the Amhara National Region is hereby issues this proclamation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

PART ONE

General

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 ዓ/ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1. Short Title

This proclamation may be cited as “The Amhara National Regional State Courts Establishment Revised Proclamation No .223/2015.”

2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

ሀ.“ምክር ቤት” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነዉ፤

ለ.“ሕገ- መንግስት” ማለት የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት ነዉ፤

ሐ.“የብሔረሰብ አስተዳደር” ማለት በሕገ-መንግስቱ መሠረት የተቋቋሙት የዋግ ኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደሮች ናቸዉ፤

መ.“ጉባዔ” ማለት የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ነው፤

ሠ.“ዳኛ” ማለት በሕግ መሠረት በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተመርጦ በምክር ቤት የተሾመ የተፈጥሮ ሰዉ ነው፤

ረ.“ሬጅስትራር” ማለት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ውስጥ አስተዳደራዊና ችሎት ነክ ተግባራትን እንዲያከናውን በጉባዔው የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ሲሆን፤ረዳት ሬጂስትራሮችን ይጨምራል፤

ሰ.“የጉባዔ ተሿሚዎች” ማለት የጉባዔ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪ፣ሬጂስትራር፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ ቃዲና በጉባኤው የሚሾሙ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ይጨምራል፤

ሸ. «የፍርድ ቤት የሥራ ኃላፊ” ማለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና ምክትል ፕሬዝደንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሳቢዎችን ያጠቃልላል፡፡

2. Definition

1. Unless the context requires otherwise in this proclamation:

a. **“Council** “ means the Amhara National Regional Council;

b. “**Constitution”** means the Revised Constitution of the Amhara National Region;

c. “**The Nationality Administration”** means the Hihimara, Awi and Oromo Nationality Administrations established as per the Constituition.

d. **“Commission**” means the Judicial Administration Commission of the Region;

e. **“Judge**” means a natural person appointed by the Council, up on the recuritmnt, as per the law, of the Judicial Administration Commission of the Region;

f. **“Registrar**” means a natural person appointed by the Commission to carry out administrative and judicial related functions in courts of the region; and includes the assistance registrar.

g. “ **Commission Appointees**” means the head of the commission office , process coordinator , registrar, defence lawyer, kadi; and shall incude other officials appointed by the commission;

h. “**Court Officials**” means president and vice president of the supreme court, president the high court; and shall include

presiding judges of the woreda court;

2. በዚህ አዋጅ ዉስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸዉ ለሴትም ጾታም በተመሣሣይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍ/ቤቶች መቋቋም፣ አደረጃጀት፣የሥራ ኃላፊዎች አሿሿም፣ ሥልጣንና ተግባር

ንዑስ ክፍል አንድ

ስለ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች መቋቋምና አደረጃጀት

3. ስለ ፍርድ ቤቶች መቋቋም

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የብሄራዊ ክልሉ ፍ/ቤቶች ተቋቁመዋል፡-
   ሀ. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤
   ለ. የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤
   ሐ. ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር፣ ከባህር ዳር ዙሪያ፣ ከይልማና ዴንሳ፣ ከጎንጂ ቆለላ፣ ከሜጫ፣ ከሰሜን አቸፈር እና ከደቡብ አቸፈር ወረዳዎች ክልል የሚቀርቡለትን የፍታብሔርና የወንጀል ክሶች በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ ተቀብሎ የማየትና ፍርድ የመስጠት ሥልጣን ያለዉ የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤እና
   መ. የወረዳ ፍርድ ቤት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ከም/ቤቱ አፈ-ጉባኤና ከርዕሰ መስተዳድሩ ጋር በመመካከር በክልሉ ም/ቤት ሲወሰን የክልሉን አስተዳደራዊ ማዋቀር ሣይጠብቅ ተጨማሪ የወረዳና የከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2. In this proclamation, any expression in the masculine gender includes the feminine.

.

PART TWO

Establishment, Organization , Appointment of Officials, Powers and Duties of Courts of the Amhara National Regional State

SUB- PART ONE

Establishment and Organization of the Amhara National Regional State Courts

3. Establishment of the Courts

1. Pursunt to this proclamation, the following National Regionl courts are established:
   a. The Regional Supreme Court;
   b. The Zone Hight Court;
   c. The Bahir Dar and Its Surrounding High Court, which entertains, as first instance and appellate jurisdiction, civil and criminal cases emanate from the territorial jurisdictions of bahir dar city, bahir dar zuria, yilmana densa, gonji kolela, mecha, north and south achefer weredas; and,
   d. The woreda court.
2. Without prejudice to the provision stipulated under sub-article /1/ of this Article; where the Supreme Court finds necessary to ensure the accessibility of judicial service, may establish, in consultation with the Speaker of the Council and the Head of Government, additional woreda and high courts, without maintaining Administrative structure of the Region.

4. የፍርድ ቤቶች ድርጅታዊ አቋም

የክልሉ ፍርድ ቤቶች ድርጅታዊ አቋም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ሌሎች ዳኞች ይኖሩታል፤
2. ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንትና ሌሎች ዳኞች ይኖሩታል፤
3. የወረዳ ፍርድ ቤት አንድ ሰብሳቢ ዳኛና ሌሎች ዳኞች ይኖሩታል፤
4. ማንኛውም ፍርድ ቤት እንደአስፈላጊነቱ ዋና እና ረዳት ሬጂስትራሮች እንዲሁም ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

ስለ ፍርድ ቤት የሥራ ኃላፊዎችና የዳኞች አሿሿም

5. የዳኞች አሿሿም

በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ /68/ ንዑስ አንቀጽ /2/ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በጉባዔው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ፡፡

6. ስለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ አሰያየም

1. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በጉባዔው አቅራቢነት በምክር ቤቱ አማካኝነት ይሰየማል፤
2. የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ አግባብ ባለው የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት አቅራቢነት በዞኑ ንዑስ ጉባዔ አማካኝነት ይሰየማል፡፡

4. Organizational Structure of Courts

The organizational structure of the courts of the region shall be as follows :

1. The Supreme Court shall have a President, vice Presidant and other judges;
2. The High Court shall have a President and other judges;
3. The wereda Court shall have a presiding judge and other judges;
4. Any court shall, as deemed necessary, have principal and assistant registrars, as well as supporting staffs necessary for its work.

SUB –PART TWO

Appointment of Officials and Judges of the Court

5. The Appointment of Judges

Judges of the Supreme Court, High Courts and Wereda Courts of the Region shall, pursuant to sub-article /2/ of article 68 of the constitution and this proclamation, be appointed by the Council up on the presentation of the Regional Judicial Administration Commission.

6. Designation of the High Court President and the Woreda Court Presiding Judge

1. The High Court President shall be designated by the Council, upon the presentation of the Commission;
2. The Presiding Judge of the Woreda Court shall, upon the presentation of the president of the Zone High Court, be designated by the Zone Sub-Commission.

ንዑስ ክፍል ሶስት

ስለፍርድ ቤት የሥራ ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር

7.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉን ፍርድ ቤቶች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ይወክላል፤
3. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን በሥራ ላይ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፤
4. የክልሉን ፍርድ ቤቶች የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
5. ዳኞችን፣ የጉባዔ ተሿሚዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በሙያቸው ይደለድላል፣ ያስተዳድራል፤
6. የጠቅላይ ፍርድ ቤቱን የማስቻያ ስፍራ ይወስናል፤
7. የፌደራሉም ሆነ የክልሉ መንግስታት ያወጧቸዉ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉስጥ ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤
8. የየደረጃው ፍርድ ቤቶች ዳኞች በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጹ ስለመሆናቸዉ በቅርብ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
9. የክልሉን ፍርድ ቤቶች የስራ አፈፃፀም ቀልጣፋና ዉጤታማ ለማድረግ የሚረዱ አዳዲስ የአሰራር ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፤

SUB-PART THREE

Powers and Duties of Officials of the Court

7. Powers and Duties of the Supreme Court President

The Presidant of the Supreme Court of the Region, being accountable to the Council, shall, by this proclamation, have the following powers and duties:

1. provide leadership to and administer courts of the region in accordance with the law;
2. Represent the Supreme Court;
3. Assign at work and administer the supreme court judges ;
4. Prepare and submit the work plan and executing draft budget of courts of the region to the council; and cause to implement same upon approval;
5. Assign and administer judges, appointees of the commission and supporting staffs, with their profession;
6. Decide the place of hearing of the Supreme Court;
7. Follow up and ensure that laws; regulations and directives issued by the Federal as well as the Regional Governments be implemented within courts of the region;
8. Follow up closely and observe that judges, at different level of courts, are molded as per societal mores and ethicatte;
9. Design new working systems which enable the performance of courts of the region be effective and efficient; and follow up the implementation of same;

10. በክልሉ ዉስጥ የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ይሠራል፤

11. በዳኞችም ሆነ በሌሎች ከፍተኛ የክልሉ መንግስት ባለሥልጣናት ሹመት አሰጣጥ ስነ-ስርዓት ላይ ተገኝቶ ቃለ-መሃላ ያስፈጽማል፤

12. የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የህግ መጽሄት እንዲቋቋምና ትምህርታዊ የሆኑ የዓመቱ ፍርዶችና ውሣኔዎች ተመርጠው እንዲታተሙ ያደርጋል፤

13. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ፕሮግራሞችና የስራ ዕቅዶች ዉስጥ የስርዓተ ጸታ ጉዳዩች ስለመካተታቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

14. በክልሉ ውስጥ ስለሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ በየስድስት ወሩ ለምክር ቤቱ ዘገባ ያቀርባል፤

15. ከህገ-መንግስቱና ከዚህ አዋጅ ጋር በማይቃረን ሁኔታ በሌሎች ሕጎች የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

8. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝደንት ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝደንት ተጠሪነቱ ለፕሬዝደንቱ ሆኖ፡-

1. በፕሬዝደንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. ፕሬዝደንቱ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

10. work in consultation with the pertinent organs in order to strengthen judicial function in the region;

11. cause the execution of oath by being present on the appointment of judges and senior government officials;

12. Cause the establishment of law journal of the supreme court; and the publication of educative judgements and decisions of the year;

13. follow up and ensure that gender is mainstreamed in the programs and plans of courts of the region;

14. Submit a performance report, in every six month, of courts of the region to the council;

15. Preform such other related duties bestowed upon him by other laws, without contrary to the constitution and this proclamation.

8. Powers and Duties of the Vice President of the Supreme Court

The vice President of the Supreme Court of the Region, being accountable to the President, shall have the following powers and duties;

1. Perform such functions as may specifically be referred to him by the president;
2. Represent the President in the absence of the latter or is unable to perform his duties.

9. ስለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና ምክትል ፕሬዝደንት ከኃላፊነት መነሳት

1.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ወይም ምክትል ፕሬዝደንት ስራዉን ሊለቅ ወይም ከኃላፊነት ሊነሳ የሚችለዉ በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ ሲወስን ወይም ጥፋት መፈጸሙ ወይም በአመራር ረገድ ጉልህ ድክመት ማሳየቱ ሲታመን ነዉ፤

2.የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ርዕሰ መስተዳድር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ወይም ምክትል ፕሬዝደንት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተዉ አኳኋን ጥፋት ፈጽሞ ወይም በአመራር ረገድ ጉልህ ድክመት አሳይቶ መገኘቱን የተረዳ እንደሆነ ለጊዜዉ ከስራ አግዶ እስከተከታዩ ምክር ቤት ጉባዔ በማቆየት ከኃላፊነት እንዲነሳ ለጉባዔዉ ያቀርበዋል፡፡ ጉባዔዉም ጥፋት ስለመፈጸሙ ወይም ጉልህ የአመራር ድክመት ስለማሳየቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት አዳምጦ አስፈላጊዉን ይወስናል፤

3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ወይም ምክትል ፕሬዝደንት በራሱ ፈቃድ ስራዉን ለመልቀቅ የወሰነ እንደሆነ ስራዉን ከመልቀቁ 3 ወር አስቀድሞ ለርዕሰ መስተዳድሩ በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ርዕሰ መስተዳድሩም ይኸዉ የጽሁፍ ማስታወቂያ እንደደረሰዉ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ /3/ ፊደል ተራ ቁጥር «ረ" ድንጋጌ መሰረት ለፍርድ ቤቱ ጊዚያዊ ኃላፊ እንዲመደብ ካደረገ በኋላ የሥራ መልቀቂያዉን ይሰጠዋል፡፡

9. Removal from Office of the President and Vice President of the Supreme Court

1. The President or Vice President of the Supreme Court may leave his post where he decides to resign on its own will or beleieved commiting misbehavior or manifest gross incompetence in his leadership.

2. Where the Head of Government of the National Regional State recognizes that the Supreme Court President or Vice President commits misbehavior or manifest gross incompetence in his leadership, pursuant to sub Article /1 of this Article, shall suspend him up to the subsequent session of the Council; the Council thereby decides on the report submitted to it as to the commission of misbehavior or manifestation of gross leadership incompetency;

3. Without prejudice to the provisions stipulated under sub-article/1/ and /2/ of this Article, where the Supeme Court President or Vice President decides to leave his office in his own will, he shall have a duty to notify the Head of Government in writing prior to 3 (three) months of leaving his office. The Head of Government shall, after assigning temporary judicial official as per sub article /3/ alphabet /f/ of Article 60 of the Constitution of the Region, render him the release upon received the notice thereof.

10. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ስልጣንና ተግባር

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ተጠሪነቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ፍርድ ቤቱን በበላይነት ይመራል ፣ ያስተዳድራል፣ ይወክላል፤
2. የፍቤቱ የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
3. የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን የማስቻያ ስፍራ ይወስናል፤
4. አስተማሪነት ያላቸው የየአመቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔዎች ተመርጠው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲላኩ ያደርጋል፤
5. ስለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥራ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በየሶስት ወሩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ፍርድ ቤቱ በብሄረሰብ አስተዳደሩ ውስጥ የተደራጀ ሆኖ ሲገኝ እንደተገቢነቱ አግባብ ላለው የብሄረሠብ ምክር ቤት ጉባኤ ዘገባ ያቀርባል፣ ጉባኤው የሚሰጠው አስተያየት ቢኖር ይህንኑ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሚልከው ሪፖርት ውስጥ ያካትታል፤
6. በዞኑ ዉስጥ የዳኝነት ስራን ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ይሰራል፤
7. በጉባኤውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንቱ የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. ከህገ-መንግስቱና ከዚህ አዋጅ ጋር በማይቃረን ሁኔታ በሌሎች ሕጎች የሚሰጡትን ተዛማጅ

10. Powers and Duties of the High Court President

The President of High Court, being accountable to the President of the Supreme Court of the Region, shall have the following specific powers and duties:

1. Provide leadership to, administer and represent the court ;
2. cause the preparation of the work plan and execution budget daft of the court; and implement same upon approval;
3. Decide the place of hearing of the High Court;
4. cause to be sent yearly selective and educative decisions of the high court to the supreme court of the region;
5. Submit a performance report, in every three months, on the judicial activities of the high court to the supreme court of the region; and to the appropriate nationality council, where the court is organized in the nationality administration; when the council renders any comment, it shall include the same in the report to be sent to the supreme court;
6. work in consultation with the pertinent organs in order to strengthen the judicial activity in the zone;
7. Implement directives rendered by the commission and president of the supreme court;
8. Preform such other related duties bestowed upon him by other laws, without contrary to the

ተግባራት ያከናውናል።

constitution and this proclamation.

11.<u>የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሣቢ ዳኛ ስልጣንና ተግባር</u>

የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሣቢ ዳኛ ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ፍርድ ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይወክላል፤
2. የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
3. የፍርድ ቤቱን የሥራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤትና ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
4. ስለ ፍርድ ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ በየሶስት ወሩ ለወረዳው ምክር ቤትና ጉዳዩ ለሚመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘገባ ያቀርባል፤
5. ዘገባውን ለወረዳ ምክር ቤት በሚያቀርብበት ጊዜ ጉባኤው የሚሰጠው አስተያየት ቢኖር ይህንኑ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚልከው ሪፖርት ውስጥ ያካትታል፤

11. <u>Powers and Duties of the woreda presiding Judge</u>

The Presiding judge of the woreda court, being accountable to the ebmbraced zone high court president shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1.Provide leadership to, administer and represent the court;

2.Recruit and administer personnel of the court;

3. prepare and submit the work plan of the court to the council of the woreda and the president of the high court; implement same upon approval;

4. Submit a report, every three months, to the woreda council and the pertinent high court as to the judicial performance of the court;

5. Incorporate comments of the Council, if there is any while presenting the report, in the report submitted to the High Court;

6. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶችና በንዑስ ጉባዔው የሚተላለፉለትን መመሪያዎች አክብሮ ይፈፅማል፤

7. በወረዳዉ ዉስጥ የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ይሠራል፤

8. ከህገ-መንግስቱና ከዚህ አዋጅ ጋር በማይቃረን ሁኔታ በሌሎች ሕጎች የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

12.ስለፍርድ ቤቶች ዘገባ አቀራረብ፣ ይዘትና የግምገማ ስርዓት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /5/ እና አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /4/ ስር በተደነገገው መሰረት እንደአግባቡ ለወረዳ ወይም ለብሔረሰብ ምክር ቤት ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ዘገባ በፍርድ ቤቶቹ መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩር ሆኖ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ.ዓመታዊ የሥራ እቅድና የተከናወኑ ተግባራት፤

ለ. የሰው ኃይል አስተዳደር ጉዳዬች፤

ሐ. የተገኙ አዎንታዊ ዉጤቶች፤

መ. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤ እና

ሠ. ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው ሌሎች ጉዳዮች፡፡

6. Implement respectfully those directives conveyed by the presidents of the supreme court of the region and of the high court, as well as by the sub-commission;

7. work in consultation with the pertinent organs in order to strengthen judicial activity in the wereda;

9. Preform such other related duties bestowed upon him by other laws, without contrary to the constitution and this proclamation.

12. Report Submission , Content and Evaluatuon Procedure of Courts

1. The report prepared and submitted to the woreda or Nationality council, as the case may be, pursuant to the provisions stipulated under sub article /5/ of Article 10 and sub a-article /4/ of Article 11, shall focus on the regular judicial activity of the courts and incorporate the following points:

a. Annual work plan and performed activities;

b. Human resource administration issues;

c. Positive results found;

d. Main problems encounterd and measures taken as a solution;

e. Other issues that need special attention.

2. የብሔረሰብ ወይም የወረዳ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ለምክር ቤቱ ዘገባ እንዲቀርብ ጉባዔው ከመካሄዱ 15 ቀናት አስቀድሞ ፍርድ ቤቱን በጽሑፍ መጠየቅ አለበት፤

2.The speaker of the nationality or the woreda council shall notify, in writing, the court prior to 15 (fifteen) days of the Assembly to submit its report;

3. ፍርድ ቤቱም ዘገባዉን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ጉባዔው ከመካሄዱ ከአምስት ቀናት በፊት ለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት መላክ ይኖርበታል፤

3. The Court shall then prepare and submit written report to the secretariat of the Council 5 days prior to the commencement of the session of same;

4. የፍርድ ቤቱ ዘገባ ለጉባዔው የሚቀርበዉ በፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት፣ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም እንደአግባቡ በወኪሉ አማካኝነት ይሆናል፤

4. The report of the court shall be submitted to the Assembly, by the president of the court, presiding judge or by the representative of the court as appropriate;

5. ጉባዔው ዘገባውን በሚገመግምበት ወቅት የሚነሱት ሀሳቦች በቅን ልቦና ላይ የተመሰረቱና የፍርድ ቤቱን የዳኝነት ነጻነት የማይጋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፤

5. When evaluating the report of the court, the assembly of the council shall raise ideas in a good faith and they shall not affect judicial independence of the court;

6. የየምክር ቤቱ አፈ- ጉባዔ የምክር ቤቱን የግምገማ ዉጤት ለክልሉ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በሪፖርት መልክ ማሳወቅ አለበት፤

6. Each speaker of the council, shall notify in a report form , the result of the councils evaluation, to the secretariat of the regional council;

7. የፍርድ ቤቱ ዘገባ በምክር ቤቱ ሲገመገም የሚከተሉትን መፈጸም የተከለከለ ነዉ፡-

7. Where the report of the court is evaluated with the council, it is prohibited to execute the followings:

ሀ. ፍርድ ቤት ለመቅረብ በሂደት ላይ ያሉ፣ ቀርበዉ በክርክር ላይ ያሉና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን ማንሳት፤

a. Raising cases to be brought or pending before courts or cases already disposed of by the court ;

ለ. የፍርድ ቤቱን ክብርና የዳኞችን ሰብዕና ሊጐዳ በሚችል አኳኋን መወያየት፤

b. Discussing on matters that may affect the dignity of the court and integrity of judges;

ሐ. የፍርድ ቤቱን ፕሬዝደንት ወይም ሰብሳቢ ዳኛ ወይም ሌሎች ዳኞችና የፍርድ ቤቱን አባላት ጉባኤው ውሳኔ ሳይሰጥ ከስራ ማሰናበት፣ ከደመወዝ የማገድ ዕርምጃ መውሰድ ወይም ደመወዝ መቁረጥ ወይም ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ፡፡

c. To dismiss, take ameasure of suspension of salary or deduct salary or shall take measures, on the president of the court or presiding judge or other judes and members of the court, where the assembly not rendering a decision.

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ስር የተጠቀሱት ጉዳዮች ተፈጽመዉ ሲገኙ አፈ-ጉባዔው በራሱ አነሳሽነት ወይም በሪፖርት አቅራቢዉ ወይም በምክር ቤት አባላት አሳሳቢነት ድርጊቱን መከልከል ወይም ማስቆም አለበት፤

9. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ለህግ አውጭው ምክር ቤት በሚያቀርባቸዉ ዘገባዎች ላይም እንደአግባብነታቸው በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

8. Where cases indicated under sub-article /7/ of this Article are found committed, the speaker shall stop or interrupt immediately such occurance upon his own initiation, with the request of the person presenting the report or with initiation of members of the council;

9.The provisions of this Article shall, *mutatis mutandis*, be applicable on reports that the president of the supreme court of the region submit to the legislative council.

ክፍል ሶስት

ስለ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን፣የችሎት አደረጃጀትና የዳኝነት ስራ አመራር

ንዑስ ክፍል አንድ

የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

13. የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በግልጽ ተለይተው በፌደራሉ መንግስት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር ከሚወድቁት ጉዳዮች በስተቀር በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 66 እና 67 እንዲሁም በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80 ላይ የተጠቀሱትን ክልላዊ ጉዳዮች በቀጥታ ወይም በይግባኝ የማየትና የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

PART THREE

Judicial power of the Courts , Organization of Division and Judicial Management

SUB-PART ONE

Judicial Power of Courts

13. Judicial Power of Courts of the Region

5. Except cases that are clearly and specifically stipulated under the jurisdiction of the courts of the federal government, courts of the Region shall exercise their jurisdiction over such indicated regional matters directly or by appeal, as provided in Article 80 of the constitution of the federal government; as well as, articles 66 and 67 of the constitution of the region;

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቶቹ በፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓትም ሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች በተደነገገው መሰረት የሚቀርቡላቸውን ክሶች በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ በመቀበል ይመረምራሉ፣ ፍርድ ይሰጣሉ፡፡

2. Without prejudice the provisions of sub-article /1/ of this Article, the courts both with a civil procedure code, or with a criminal procedure code, as well as, pursuant to other laws, shall receive and investigate charges either with first instance or in appeal; and thereby render judgement.

14. <u>ስለ ወረዳ ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን</u>

14. <u>Civil Jurisdiction of the Woreda Courts</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ /13/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የወረዳ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች ሕጎች መሰረት የሚቀርቡላቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች በቀጥታ ወይም በይግባኝ ተቀብለው የመዳኘት ስልጣን አላቸው፤

1.Without prejudice to the general provision stipulated under Article /13/ of this proclamation, the woreda courts of the region shall have a jurisdiction on civil cases as first instance or in appeal , pursuant to the civil procedure code and by other laws;

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የወረዳ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ጉዳይ ያላቸው የስረ-ነገር ዳኝነት ስልጣን፡-

2.Notwithstanding the provision of sub-articl /1/ this Article, the woreda courts shall have a material juridiction on civil cases:

ሀ. በሚንቀሳቀስ ንብረት እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺህ ብር)፤ እና

a. all suits regarding movable property where, the amount involved does not exceed 300,000 /three hundred thousand / Ethiopian Birr; and

ለ. በማይንቀሳቀስ ንብረት እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ግምት ባላቸው ጉዳዮች የተወሰነ ይሆናል፡፡

b. All suits regarding immovable property, where the amount involved does not exceed 500,000 /five hundred thousand/ Ethiopian Birr.

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳ ፍርድ ቤቶች ወላጅነትን፣ አካልን ነፃ ማውጣት (ሐብየስ ኮርፐስን) እና ሌሎች ዋጋቸው በገንዘብ የማይገመት ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮችን የመቀበልና የመዳኘት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

3. Without prejudice to the provisions stipulated under sub- article /1/ and/2/ here in above of this Article, the woreda courts shall exercise jurisdiction over filiation, *habeas corpus* and other cases the subject matter of which can not be expressed in money.

15.የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን

1.የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ-ስርዓት ህግ እና በሌሎች ሕጎች መሠረት የሚቀርቡላቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ የመቀበልና የመዳኘት ሥልጣን አላቸው፤

2.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ ቢኖርም ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሄር ጉዳይ ያላቸው የስረ-ነገር ዳኝነት ስልጣን፦

ሀ. በሚንቀሳቀስ ንብረት ከብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) በላይ፤እና

ለ. በማይንቀሳቀስ ንብረት ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በላይ የገንዘብ ግምት ባላቸው ጉዳዮች የተወሰነ ይሆናል፡፡

16.ስለ ይግባኝ ስርዓት

በማናቸውም ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ከቀረበና ከተመረመረ በኋላ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙን ላቀረበው ወገን የመጨረሻ ይሆናል፡፡

17.ስለ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ሥልጣን

1. በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሶስት ዳኞች ለሚሰየሙበት አጣሪ ችሎት ከቀረበና ችሎቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ያመነ እንደሆነ ነው፤

15. The Civil Jurisdiction of the Zone High courts

1.The zone high courts shall have a jurisdiction on civil cases as first instance or in appeal , pursuant to the civil procedure code and by other laws;

2.Notwithstanding general provision of sub-article /1/ of this Article, the material juridiction of the high court on civil cases:

a. Regarding movable property where the amount involved exceeds 300,000/three hundred thousand/ Ethiopian Birr; and,

b. Regarding immovable property where the amount involved exceeds 500,000 /five hundred thousand/ Ethiopian Birr.

16. Right of Appeal

Judgements, on any matter grievances lodged thereon, renderd by the appellate court shall be final with regards to the appellant.

17. Judicial Power of the Cassation Bench of the Supreme Court

1. A final decision shall be heard in cassation subject to prior ruling as to the existence of fundamental error of law, and believed qualifying for cassation by a screening division/bench/ wherein three judges of the supereme court sit;

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ታይቶባቸዋል የሚባሉትንና የሚከተሉትን ክልላዊ ጉዳዮች ተቀብሎ በሰበር ለማየትና ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-
   ሀ. በወረዳ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች፤
   ለ. በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠባቸው ክልላዊ ጉዳዮች፤ እና
   ሐ. በጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ታይተው የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠባቸው ክልላዊ ጉዳዮች፡፡

2.The cassation bench of the regional supreme court shall have a jurisdiction to entertain and decide on the following regional cases which have a fundamental error of law:
   a. Cases that have been given a final decision, in appeal, by the woreda court;
   b. Regional cases that have been given a final judgement by the high court; and
   c. Regional cases that have been given a final judgement, by a regular bench of the Supreme Court.

3. በሰበር እንዲታይ የሚቀርብ ማናቸውም አቤቱታ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሥርዓቶች ሊያሟላ ይገባል፡-
   ሀ. አቤቱታ የሚያቀርበው ተከራካሪ ወገን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በአቤቱታው ጹሑፍ ውስጥ በዝርዝር ማቅረብ ይኖርበታል፤
   ለ. አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔና የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዮ ላይ የሰጡትን ውሣኔ ግልባጭ ከሰበር አቤቱታው ጋር ማያያዝ አለበት፡፡

3. Any application to be heard in cassation, shall fulfill procedures stated herein under:
   a. applicant shall explain ,in detail, in his application the reason why fundamental error of law is committed;
   b. the applicant shall attach thereto the application, the decision which is the ground of complaint and the copies of decisions renderd by lower courts on the matter thereof;

4. የሰበር አቤቱታ የሚቀርበው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘበት ወይም ውሳኔው በይፋ ከተነገረበት ዕለት ጀምሮ በሚታሰብ በ90 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው፤

4. the application of cassation shall be submitted within 90 (ninety) days from the date on which final decision is renderd or commencing from the date the decision is officially declared;

5. የሰበር ሰሚ ችሎቱ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደአስፈላጊነቱ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሁለት
በየደረጃው ስላሉ ፍርድ ቤቶች የችሎት አደረጃጀት

18.ስለ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት አደረጃጀት

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ. የፍትሐብሔር ችሎት፤
   ለ. የወንጀል ችሎት፤እና
   ሐ. የሰበር ሰሚ ችሎት።

2. በእያንዳንዱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔርና የወንጀል ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ፤ ሆኖም በሰበር ሰሚ ችሎት አንድ ሰብሳቢና አራት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/-/2/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ።

19.ስለከፍተኛ እና የወረዳ ፍርድ ቤት ችሎቶች አደረጃጀት

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የዞን ከፍተኛ እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች በየበኩላቸው በፍትሐብሔርና በወንጀል ችሎቶች ይደራጃሉ፤

5. The cassation bench may confirm, vary of reverse the decision on which the application is lodged.

SUB-PART TWO
Organizationa of Divisions of Courts with Different Levels

18. Organaiztion of divisions of the Supreme Court

1. The Regional supreme court shall have the following Divisions:
   a. The civil Division;
   b. The criminal division ;and
   c. The cassation Division.

2. There shall sit a presiding judge and two judges in each civil and criminal divisions of the Supreme Court; in a cassation division; however, there shall sit a presiding judge and four judges.

3. Without prejudice to the provisions stipulated under sub-articles /1/-/2/ of this Article, the president and vice president of the Supreme Court, may sit as a presiding judge of the Supreme Court division.

19. Organization of Divisions of the High and Woreda Court

1. The Zone high and the woreda courts of the region shall be organized in the civil and criminal divisions;

2.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቶቹ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ ለተወሰኑ ጉዳዮች ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጁ ይችላሉ፤

3.እያንዳንዱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ችሎት በአንድ ሰብሳቢና በሁለት ዳኞች ያስችላል፡፡

20.ስለዳኝነት ዉሳኔ አሰጣጥ

1. ሶስት ወይም እንደአግባብነቱ አምስት ዳኞች ሆነዉ በሚያስችሉበት በየትኛውም ችሎት በዉሳኔ አሰጣጥ ረገድ ዳኞች የሀሣብ ልዩነት ያጋጠማቸው እንደሆነ አብዛኞቹ በአብላጫ ድምጽ የደገፉት ሀሣብ የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ይሆናል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የአነስተኛዉ ድምጽ የልዩነት አስተያየት በመዝገቡ ላይ መስፈር ይኖርበታል፡፡

2. Notwithstanding the provision of sub-article /1/ of this Article, the courts may organize additional divisions/benches/ for the particular cases in order to make the jursdicial activity accessible and effective;

3. There shall sit a presiding judge and two judges in each civil and criminal division of the High Court.

20. Judicial Decisions

1. In the absence of unanimity in renedering a decesion of any hearing held by three or five judge, as deemed necessary, the decision of the majority shall be the decision of the court;

2. Notwithstanding sub-article /1/ of this Article, the dissenting opinion of the minority vote shall be recorded in the file thereon.

ንዑስ ክፍል ሦስት
የዳኝነትና ከዳኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አመራር

21. የማስቻያ ስፍራ

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ የማስቻያ ቦታ በባሕር-ዳር ከተማ ይሆናል፤
2. የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች መደበኛ የማስቻያ ቦታ የየዞኑ ወይም ብሄረሰብ አስተዳደሩ ርዕሰ ከተማ ይሆናል፤
3. የወረዳ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ቦታ ፍርድ ቤቶቹ የተከፈቱበት ስፍራ ይሆናል፤

SUB-PART THREE
Judicial Management and Related Cases

21. Place of Hearing

1.The regular place of hearing of the supreme court shall be in Bahir Dar;

2. The regular place of hearing of the high courts, shall be at the capital of each zone or nationality administration;

3. The place of hearing of woreda courts shall be at places where the same are established;

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /3/ የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በየትኛውም እርከን ላይ የተቋቋመ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡን ለህዝቡ ተደራሽና ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሥልጣን ክልሉ ውስጥ ተዘዋዋሪ ችሎት ወይም እንደተገቢነቱ በየትኛውም ስፍራ ቋሚ ችሎት በማደራጀት ሊሠራ ይችላል።

22. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

1. ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን በግልጽ ችሎት ያከናውናሉ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተመለከተው ቢኖርም ለዳኝነት አሠራር አግባብ ያላቸው የሥነ-ሥርዓት ሕጎች የሚደነግጉት እንደተጠበቁ ሆኖ፤

ሀ. ለተከራካሪዎች የግል ሕይወት፣

ለ. ለሕዝብና ለመንግስት ደህንነት፤

ሐ. ለመልካም ጠባይ ወይም ለግብረ-ገብነት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት፤ እና

መ.ሕጻናት ተከሰዉ ወይም ምስክሮች ሆነዉ ሲቀርቡ ፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት ያስችላሉ።

23. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

1. በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ /5/ ንዑስ አንቀጽ (2) እና በዚህ አዋጅ መሠረት የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፤

4. Without prejudice to the provisions stipulated from sub-article /1/ upto sub-article /3/ of this Article, a court established at any level may organize a permanent or circuit bench, as deems appropriate, at any place within its jurisdiction where it finds necessary to make the judicial service accessible to the public and effective thereof.

22. Open Hearing

1. Judicial activities shall be conducted in open court.
2. Notwithstanding the provision of sub-article/1/ of this Article, and without prejudice to other relevant procedural laws relating to judicial proceedings, courts may hear in camera where it is beleived necessary for the:

a. Personal life of the parties,

b. public and state safety and security,

c. public morality and decency; and,

d. where children appear as a defendant or witness.

23. Working Language of the Courts

1.Amharic shall, pursuant to Article 5 sub-article /2/ the revised regional constitution and this proclamation, be the working language of the national regional state courts;

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም በብሔረሰብ አስተዳደሮች ውስጥ የፍርድ ቤቶችን የስራ ቋንቋ አግባብ ያለው የብሄረሰብ ምክር ቤት ሊወስን ይችላል፤

3. የፍርድ ቤቱን የስራ ቋንቋ መናገር ለማይችልና አስተርጓሚ ይዞ ላልቀረበ ባለጉዳይ ፍርድ ቤቶች አስተርጓሚ ይመድባሉ።

24. ከችሎት ስለመነሣት

1. የማናቸውም ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ጉዳዮች በአንዱ ምክንያት ከችሎት ይነሳል፡-

   ሀ. ዳኛዉ ከተከራካሪዎቹ መካከል ከአንደኛዉ ወገን ወይም ከጠበቃዉ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለዉ እንደሆነ፤

   ለ. ዳኛዉ ከተከራካሪዎቹ የአንደኛዉ ወገን ሞግዚት ወይም ነገረ-ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ፤

   ሐ. ዳኛዉ ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ መንገድ ያየዉ ወይም የሚያዉቀዉ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤

   መ. ዳኛዉ ከተከራካሪ ወገኖች ከአንደኛዉ ወይም ከጠበቃዉ ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለዉ እንደሆነ፤

2. Notwithstanding the provision stipulated under sub-article /1/ herein above, the relevent nationality council may decide the working language of courts with in the nationality administrations;

3. Courts shall assign an interpreter to a party that can not speak the working language of the court, and could not bring his own interpreter.

24. Withdrawal of Judges

1. A judge of any court shall withdraw fron a sit in one of the following reasons :

   a. Where the judge is related to one of the parties or the advocate thereof by consanguinity or by affinity;

   b. where the dispute relates to a case in which one of the parties is a person for whom he acted as tutor, legal representative or advocate;

   c. Where he has previously acted in some capacity as judge or arbitrator in connection with the case or the subject matter of the dispute;

   d.Where he has a case pending in court with one of the parties or the advocate thereof;

ሠ. ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች ስር ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ ሊሰጥ አይችልም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባዉ መሆኑን ሲያዉቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ መተካት ይኖርበታል፡፡

25. ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት

1. ከተከራካሪዎች አንደኛው በአንቀጽ /24/ በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሰረት አንድ ዳኛ ከችሎት መነሳት የሚገባዉ መስሎ የታየዉ እንደሆነ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤቱ በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፤

2. ማመልከቻዉ የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል፤

3. አንድ ዳኛ ብቻዉን የሚያስችል ከሆነ ከችሎት ስለመነሳት የሚቀርብለትን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄዉን የተቀበለዉ እንደሆነ ይነሳል፡፡ ጥያቄዉን ያልተቀበለዉ እንደሆነ ግን በዚያዉ ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፣ ሌላ ችሎት ከሌለ ደግሞ እንደአግባቡ በዚሁ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ወይም ሰብሳቢ ዳኛ እንዲወሰን ማስተላለፍ አለበት፤

e. where there are sufficient reasons, other than those specified under sub article /1 / /a/to /d/ hereof, to conclude that injustice may be done.

2. The judge concerned shall withdraw as soon as he is aware that he should not sit, in accordance with sub Article /1/ hereof, and shall be replaced by another judge.

25 Application for Withrawal of Judge

1. Where a party to a case is of the opnion that a judge should not sit for one of the reasons specified in article 24 hereof, he may submit a written application to the court requesting that the judge be removed,

2. The application shall be made before the trial opens or soon after the party becomes aware of the reason for making such application;

3. Where the judge is sitting alone, he shall, after considering the application, either withrdaw or refer the matter for decision to another division of the same court or where there is no other division to the president or presiding judge, as deemed appropriate;

4. ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር የሚያስችል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ማመልከቻው የቀረበበት ዳኛ በሌለበት ጉዳዩ በቀሪዎቹ ዳኞች ታይቶ ዉሳኔ ያገኛል፤ይሁንና በቀሪዎቹ ዳኞች መካከል ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ ጉዳዩ በሌላ ችሎት እንዲታይ ይደረጋል፤

4.Where the judge is sitting with other judges, he shall withdraw and the remaining judges shall hear the case application and give a decision thereon; if there is a disagreement between the remaining judges, however, the shall be entertained by another division;

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል፤

5.A decision given under sub-article /3/ and /4/ hereof shall be final and subject to no appeal;

6. የሚሰጠዉን ማናቸውንም ውሳኔ ዳኛዉ ወዲያውኑ ተቀብሎ መፈጸም አለበት፡፡

6.A judge shall forthwith comply with a decision given under this article.

26. የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሥልጣንና ተግባር

26.Powers and Duties of the Process Coordinator

በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚገኘውና ከችሎት ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት የሚመራው ማንኛውም የሥራ ሂደት አስተባባሪ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

Any process coordinator, who directs judicial related activities in courts found at different level, shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powes and duties:

1. የሂደቱን የመግባቢያ ሰነድ ወይም ቲም ቻርተር ከሂደቱ አባላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤

1. Prepare the memorandum of understanding or team charter of the process together with members of the process;

2. የሥራ ሂደቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ሲጠየቅም የሥራ አፈጻጸም ዘገባ ያቀርባል፤

2. Prepare work plan of the process; follow up its implementation; and submit a performance report where requested;

3. በቅደም ተከተል በሚቀመጠዉ የጉዳዮች አስታንዳርድ መሠረት ለእያንዳንዱ የሂደቱ አባል የሥራ ስምሪት በመስጠት አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

3. provide activities to each member of the process as per sequencially laid down standard of cases; and follow up its implementation;

4. የሂደቱን ሥራዎች በበላይነት

4. Coordinate the activities of the process and

ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

render support thereto;

5. ጠንካራና ደካማ አፈፃፀሞችን በመለየት ችግር ፈች በሆኑ ሃሣቦች ላይ የሂደቱን አባላት ያወያያል፣ የመዝገቦችን ብዛትና ፍሰት እያጠና የተሻለ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ለፍርድ ቤቱ የስራ ኃላፊ ሃሳብ ያቀርባል፤

6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሂደቱን በመወከል በተለያዩ ስብሰባዎች ይካፈላል፤

7. የሂደቱ ተግባራት በወጣላቸው ቅደም ተከተል መሰረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

8. በሂደቱ ስር በሚገኙ ችሎቶች የሚያስችሉ ዳኞች ተሟልተው ማስቻላቸውንና ሀላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

9.ከባለጉዳዮች በኩል የሚቀርቡና ከመዛግብት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ እንደ አስፈላጊነቱ መፍትሄ ይሰጣል ወይም ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ያስተላልፋል፤

10. የሥነ-ምግባር ጉድለት የሚያሳዩትን የሂደቱን አባላት በመለየት እንደአግባቡ ለዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽህፈት ቤት ወይም ለሰው ኃይል ሥራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት ለዲሲፕሊን ያቀርባል፤

11. በፍርድ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

27. <u>የሬጂስትራር ሥልጣንና ተግባር</u>

በየደረጃዉ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚገኝ ማንኛውም ሬጂስትራር የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

5. Discuss members of the process on problem solver ideas, by identifying strong and weak performaces; provide a proposal, through conducting a research as to the number and flow of cases, to official of the court in order to put in place a better working procedure;

6. Participate in different meetings representing the process, where it is found necessary;

7. Ensure that the process activities shall be implemented as per their sequencial order;

8.Follow up and supervise that judges in the divisions found under the process properly discharge their responsiblities;

9. Receive various complaints, related with court files, submitted from the parties; render a solution or refer the case to the pertinent body, as deems necessary;

10. Identify members of the process who manifest breaches of ethical standards, and submit same for discipline to the office of the judicial administration commission or to the human resource managenment support process, as deems appropriate;

11. Perform such other related activities rendered to him by court officials.

27. <u>Power and Duty of the Registrar</u>

Any registrar, found in different level courts, shall have the following particular powers and duties:

1. በፍትሐብሔርና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓትም ሆነ በሌሎች ሕጐች ለሬጅስትራር የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

1. Perform activities rendered to the registrar under the civil and criminal procedure codes as well as by other laws;

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሬጂስትራሩ፡-

2. Without prejudce to the general provision stipulated under sub-article /1/ of this Article , the registrar:

ሀ. ለፍርድ ቤቱ የሚቀርቡት አቤቱታዎች፣ ክሶችና ይግባኞች በህጉ የተቀመጠውን መሥፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

a. Ensure that applications, statement of claims and defence as well as appeals satisfy sufficiencies provided in the law;

ለ. የክስና ይግባኝ ፋይሎች እንዲከፈቱ ይመራል፣ ለዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል እንዲያመች የተጠየቀዉን ዳኝነት በመለየት ያስተላልፋል ፣ መልስ ያቀባብላል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ጋር በመመካከር የቀጠሮ ፖሊሲዎችን ይተገብራል፣ያስተገብራል፤

b. Refer statement of claim and defence as well as appeal files to be opened; identify the relief requested for the purpose of payment of court fee and transfer thereto; receive statement of defence; implement and cause to implement adjornment policy, inconsultation with pertinent bodies;

ሐ. በመዛግብት ላይ በችሎት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ፈርሞ ወጭ ያደርጋል፤

c. Sign and cause to be dispatched orders rendered by benches on the files;

መ. ከሚያስተዳድራቸዉ ተንቀሣቃሽና የተዘጉ መዛግብት የሚጠየቁ መረጃዎችን በተመለከተ አግባብነቱን እየመረመረ የጽሁፍ ማረጋገጫ ይሰጣል፤

d. Render written confirmation, by scrutinizing its appropriateness, on informatins requested from the live and dead files that he administered thereof;

ሠ. የችሎት አስተዳደር ሥራዎች በየዕለቱ መከናወናቸዉን ይከታተላል፣ የሚያጋጥም የአሰራር ክፍተት ቢኖር ከስራ ሂደት አስተባባሪው ጋር በመመካከር መፍትሄ ይሰጣል፤

e. Follow up the daily implementation of the judicial administrative activities; render a solution thereto where procedural gap will encounter, inconsultation with the coordinator of the process;

ረ. ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የችሎት አስተዳደር ስራ እንዲኖር ችግር ፈቺ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ተገቢው የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን በቅርብ ይከታተላል፤

ሰ. በሂደቱ ውስጥ የሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን ይመራል፣ ኃላፊነታቸዉን መወጣቸዉን ይከታተላል፣ የአሰራር ችግር ሲያጋጥም መፍትሄ ይሰጣል፤

ሸ. በፕሬዝደንቱና በስራ ሂደት አስተባባሪው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

ክፍል አራት

ስለ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ መቋቋም

28. ስለ መቋቋም

በክልሉ ውስጥ ከዳኝነት ተግባር ጋር የተያያዙ ችግሮችንና ሕግ-ነክ ጉዮችን በመመርመር ለምክር ቤቱ ሀሣብ የሚያቀርብ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ከዚህ በኋላ «ጉባዔዉ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

29.ስለ ጉባኤው አባላት ጥንቅር

1. ጉባዔው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጣ ይሆናል፡-

ሀ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት----ሰብሳቢ፣

ለ. የጠቅላይ ፍ/ቤት ምክትል ፕሬዝደንት----- አባል

ሐ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶች_____አባላት፤

f. Create problem solving ideas that help establish efficient and effective judicial administrative activity; cause to put in place proper work procedure; follow up closely the implementation of same.

g. Provide leadership to support staffs of the process; follow up whether they discharge their responsibilty; render a solution where problem encounterd thereon.

h. Perform such other related activities rendered to him by the president and the process coordinater.

PART FOUR

Establishment of the Plenum of the Regional Supreme Court

28. Establishment

The Plenum of the Supreme Court (herein after called “the Plenum”), which examines and submits recommendation to the Regional Council concerning problems related to judicial functions and legal affairs, is hereby re-established by this proclamation.

29. Composition of the Members of the Plenum

1. The composition of the plenum is as follows:

a. President of the Supreme Court..... chair person,

b. Vice President of the Supreme Court.....member,

c. Judges of the Supreme Court and Presidents of the High Court.....members,

መ. በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት የሚመደብ የፍርድ ቤቱ ሰራተኛ _____ ፀሐፊ።

2. በጉባዔው ላይ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ይሳተፋል፣ ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ያልተጠቀሱ ዳኞች እና አግባብ ያላቸዉን የክልሉን መንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ ማህበራት፣ ድርጅቶች፣ የሕግ ፋኩሊቲዎች እና የሳይንስ ተቋማት የሚወክሉ ሌሎች ሰዎች እንዲሳተፉ በጉባዔዉ ሊጋበዙ ይችላሉ። ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

30. ስለጉባኤው ስልጣንና ተግባር

ጉባኤዉ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዳኝነት ሥራ አስተዳደር ረገድ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ አስፈላጊ መፍትሄዎችን መስጠት፤
2. በክልሉ ዉስጥ የዳኝነት ሥራን ለማሻሻልና በሁሉም ፍርድ ቤቶች ተመሣሣይ የህግ አፈፃፀም መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ማዉጣትና በተግባር ላይ መዋላቸውን መከታተል፤
3. አዳዲስ ህጎች እንዲወጡ ወይም በስራ ላይ ያሉ ነባር ህጎች እንዲሻሻሉ ለምክር ቤቱ ሀሣብ ማቅረብ፤
4. የክልሉን የዳኝነት ሥራ አካሄድ ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፣ እና

d. The Worker of the Supereme Court assigned to by the president..... secretary.

2. The Head of Justice Bureau of the region shall participate in the sessions of the plenum, without, however, having the right to vote.

3. Judges not referred to under sub article /1/ hereof and representatives of appropriate government offices of the region , associations, organizations, law faculities, and scienitific institutions or other individuals may be invited to participate in the plenum without, however, having the right to vote.

30. Powers and Duties of the Plenum

The Plenum, pursuant to this proclamation, shall have the following particular powers and duties:

1. Deliberate on problems encounterd in the judicial administration and work out remedies thereon;
2. Issue directives to ensure the uniform application of law in all courts of the region; and follow up the implementation of same;
3. Submit proposals to the Council for the enactment of new laws or the amendment of exisiting ones ;
4. Perform such other functions help to make the judiciary of the Region efficient and strong;

5. የራሱን ውስጣዊ የስራ ማከናወኛ መመሪያ ማዉጣት፡፡

31. የጉባዔው የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ጉባዔው መደበኛ ሥብሰባውን በዓመት ሁለት ጊዜ ያካሂዳል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል፤
2. ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አባላት መካከል 2/3ኛው በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዐተ-ጉባዔ ይሆናል፤
3. የጉባኤው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ሀሣብ የጉባዔው ውሣኔ ይሆናል፤
4. ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ጉባዔዉ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

32. ቃለ መሐላ

1. ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ከዚህ በታች የተመለከተውን ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ፡-

"እኔ አቶ/ወ/ሮ..... በዛሬው ዕለት የ ------- ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ኃላፊነት፣ በከፍተኛ ሥነ ምግባር፣ በታማኝነት እና በሕግ መሠረት ለመወጣት ቃል እገባለሁ"፡፡

5. Issue directives concerning the execution of its own duties thereof;

31. Time of Meeting and Decision Making Procedure of the Plenum

1. The Plenum shall hold its regular meeting twice a year; however, it may hold extra-ordinary meeting, as may be necessary;

2. The quorum shall be held, where two-third members, having the right to vote, are present in the meeting;

3. The decisions of the Plenum shall pass by majority vote; however, in the case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;

4. Without prejudice to the provisions stipulated herein above, the Plenum shall issue its own meeting procedure.

PART FIVE
MISCELLANEOUS PROVISIONS

32. Oath

1. Judges shall take the following oath prior to assuming their duties:

"I .....,upon my appointment and assumption of duty as judge of --------- Court, on this day, pledge to discharge with high level of judicial conduct and dedication as well as pursuant to the law the heavy responsibility entrusted to me."

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ስር የሰፈረው ቃለ መሐላ አፈፃፀም የሚከናወነው በሚከተሉት አካላት ፊት በመቅረብ ይሆናል፡-

ሀ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እንዲሁም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና ዳኞች በክልሉ ምክር ቤት ፊት፤

ለ. የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች (ሰብሳቢውን ጨምሮ) በየተመደቡባቸው ወረዳ ምክር ቤቶች ፊት፤ እና

ሐ. በብሔረሰብ አስተዳደር በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተመደቡ ዳኞች አግባብ ባላቸው የብሔረሰብ ምክር ቤቶች ፊት፡፡

2. The Oath stipulated under the provision of sub-article /1/ of this Article hereof, shall be conducted before the followung bodies:

a. The Supreme Court judges as well as the President and judges of High Court ,before the Regional Council;

b. The Woreda Court judges (including the presiding judge) , before the Woreda Councils in which they are assigned;

c. Judges assigned to courts found in the Nationality Administration, before the appropriate Nationality Councils.

33. ስለ ፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች

ማንኛውም ሰው፣ መንግስታዊ አካልም ሆነ የግል ድርጅት በክልሉ ውስጥ የተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸውን ውሣኔዎችና ትዕዛዞች የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

33. Court Decisions and Orders

Any person, government body and private organization shall have a duty to respect and implement decisions and orders renderd by Courts established in the region.

34. ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች

1. የሚከተሉት ህጐች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 11/ 1988ዓ.ም፤

ለ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 68/ 1994 ዓ.ም፤

34. Repealed and Inapplicable Laws

1. The following laws are repealed by this proclamation:

a. A proclamation issued to provide for the establishment of Courts of the Amahara National Regional State No. 11/1995;

b. The Amgara National Regional State Courts (Amendment) proclamation No. 68 /2002,

ሐ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣዉን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 153/2000 ዓ.ም፤

መ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ/ም፣

ሠ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች እንደገና ማሻሻያ (አስቀድሞ እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር 201/2005 ዓ.ም፤እና

ረ. የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 210/ 2006 ዓ.ም።

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

35. በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በማናቸውም እርከን ላይ ባለ የክልሉ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ መታየታቸውን ቀጥለው ፍፃሜ ያገኛሉ።

36. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸዉ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝደንት

c. A Proclamation Issued to provide for the Re-amendment of the Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation No. 153/2008;

d. The Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation Re-amendment Proclamation No. 169/2010;

e. The Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation Re-amendment proclamation (as amended before) Proclamation No. 201/2012; and

f. The Bahar Dar and its Surrounding High Court Establishment Proclamation No. 210/2014.

2. Any Law, Regulation, Directives or Customary Practice shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

35. Pending Cases

Pending cases, entertained in Courts found at different levels prior to the coming into force of this Proclamation, shall be disposed by the laws applicable thereon.

36. Effective Date

This Proclamation shall come in to force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazzettee of the Regional State.

Done at Bahir Dar,

This 3rd day of February, 2015

Gedu Andargachew

President of the Amhara National Region